# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 236 ህዳር 13 2005 ገጽ 1


የተከበራችሁ የአገራችን ዜጎች የሚረዳን ማንም የለም። ክብራችንና ነፃነታችንን የምናስመልሰው እኛው ብቻ ቆርጠን በመታገል ነው።ነፃነታችንን ከዚህ ወይም ከወዲያ ማዶ መጥቶ የሚሰጠን ማንም የለም። ነፃነታችን በእጃችን ነች።ሞት ወይም ነፃነት ማለት ካልቻልን ነፃነት እንዲሁ በደጅ ጥናት የምትገኝ አይደለችም።

ከግንቦት 7 ዕርስ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ሀዉልት ሊፈርስ ነዉ ተባለ

ለኢትዮጵያና ለህዝቦቿም ሆነ ለታሪኳ ምንም ደንታ የሌላቸዉ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የባቡር ሀዲድ ልንሰራ ነዉ በሚል ሰበብ ለኢትዮጵያ አንድነት፤ ነፃነትና ክብር ሲሉ በፋሺስት ጣሊያን ጥይት ተደብድበዉ የሞቱትን የታላቁን ሰማዕት የአቡነ ጴጥሮስን ሀዉልት ለማፍረስ በዝግጅት ላይ መሆናቸዉን የአዲስ አበባ ዘጋቢያችን የከተማይቱን አስተዳደር ጸ/ቤት ጠቅሶ በላከልን ዜና ገለጸ። ይህንን በኢትዮጵያ ህዝብ የትግልና የመስዋዕትነት ታሪክ ዉስጥ እጅግ በጣም ከፍተኛ ቦታ ያለዉንና ለመናገሻ ከተማችን ለአዲስ አበባ ከፍተኛ ዉበት ያጎናጸፈዉን ሀዉልት እንዲፈርስ ዉሳኔ ያሳለፉት የወያኔ ዘረኞች ሲሆኑ ይህንን ጸረ አገርና ጸረ ታሪክ ዉሳኔ ለህዝብ ያሳወቀዉ ደግሞ የአዲስ አበባ አስተዳደር ጽ/ቤት ነዉ።

ከሰሞኑ ሸገር ኤፍ ኤም በተባለዉ ሬድዮ ጣቢያ ላይ ቀርቦ የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት ሊፈርስ ነው ብሎ መግለጫ የሰጠዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ሀላፊ ..... የአቡነ ጴጥሮስ ሀዉልት ከባቡር ሀዲድ ስራ ጋር በተያያዘ ይነሳል ካለ በኋላ ሀዲዱ ከተሰራ በኋላ ሀዉልቱ ቦታዉ ላይ ተመልስሶ ይተከላል ብሏል:: ሆኖም ከዉስጥ አዋቂ ምንጮች በተገኘዉ መረጃ መሠረት የሀዲዱ ማስተር ፕላንና ዲዛይን ላይ ለሚፈርሰው የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት ምንም ቦታ ስላልተሰጠዉ ሀዉልቱ አንዴ ከፈረሰ ተመልሶ የመተከል ዕድሉ የጨለመ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የአቡነ ጴጥሮስ ሀዉልት የተሰራዉ አቡኑ በጥይት በተደበደቡበትና የመጨረሻ ትንፋቸዉን በተነፈሱበት ቦታ ስለሆነ ሀዉልቱን ከዚህ ታሪካዊ ቦታ ማንሳት ታሪክን ማርከስ ነዉ ያሉ አንድ የታሪክ ምሁር በሌሎች አገሮች ዉስጥ ምንም አይነት ” (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኢሳትን አያችሁ የተባሉ ወታደሮች ታሰሩ፤ ሠራዊቱ ዉስጥ የተፈጠረዉ መከፋፋል አሁንም እንደቀጠለ ነዉ

ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ በባድሜ ግንባር ወታደራዊ ከበባቸዉ ዉስጥ ቁጭ ብለዉ በናይልሳት የሚተላለፈዉን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንን ሲከታተሉ የተገኙ በርካታ ወታደሮች ለሁለት ሳምንታት ታስረዉ በከባድ ማስጠንቀቂያ መለቀቃቸዉን ትግራይ ዉስጥ የሚገኙ ወታደራዊ ምንጮቹን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ። አንድ ስማቸዉና ማዕረጋቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁ ከፍተኛ መኮንን በስልክ ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት ወታደሮቹ የታሰሩት በከበባቸው ውስጥ ቁጭ ብለዉ የኢሳትን ዝግጅት ሲከታተሉ ሲሆን ከ 14 ቀናት እስርና እንግልት በኋላ የተፈቱት የዲሻቸውን አቅጣጫ ወደ ናይል ሳይት ያዞሩት ሳያዉቁ በስህተት መሆኑን ለበላይ አለቆቻቸው ተናግረዉ ዳግመኛ ኢሳትን እንደማይመለከቱ ቃል ከገቡ በኋላ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዚያዉ ከባድሜ ግንባር አንድ ሌላ ከፍተኛ የጦር መኮንን ለኢሳት በሰጡት መረጃ መሠረት በመከላከያ ሠራዊቱ ዉስጥ ከፍተኛ የሞራል ዉድቀት የሚታይ ሲሆን ከዚህ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ሲጀመር በህዝብ ያልታወቀው የህውሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠናቀቀ ተባለ

ከህዝብ እይታ በተሰወሩና በርካታ ምስጢራዊ ስብሰባዎችን በማከናወን የሚታወቀው ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሃት) መቀሌ ዉስጥ የጠራዉ የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ከሦስት ቀን ዉሎ በኋላ መጠናቀቁን በአገዛዙ ቁጥጥር ስር የሚገኙት መገናኛ ብዙሃን አስታውቁ። ይህ ሲጠናቀቅ እንጂ ሲጀመር ለህዝብ ያልተገለጸዉ ስብሰባ የተነጋገረበት አጀንዳ ምን እንደሆነ በዉል ባይታወቅም ግንባሩ ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ ቀፎዉ እንደተመታ ንብ መበታተን በመጀመሩ የዚህ ስብሰባ አጀንዳም በመፍረስ ላይ ያለዉን ግንባር ከማይቀረዉ ዉድቀቱ ለማዳን ነዉ ሲሉ ብዙዎች ህወሀትን በቅርብ የሚያዉቁ የፖለቲካ ተንታኞች አስተያየታቸዉን በመስጠት ላይ ናቸዉ። ህወሀትን ጨምሮ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የመለስ ዜናዊ መታመም ከተሰማበት ግዜ ጀምሮ በመካከላቸዉ በተፈጠረዉ አለመተማመንና የስልጣን ሽኩቻ የተነሳ አብዛኛዉን ግዜያቸዉን የሚያጠፉት በስብሰባ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛዉ የአገሪቱ የመሪነት ቦታ ከእኛ እጅ በፍጹም መዉጣት የለበትም ሲሉ የነበሩት ከፍተኛ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የወያኔ አገዛዝ ፖሊሶች በኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸሙ ያለውን ኢሰብአዊ ተግባር እንዲያቆሙ ተጠየቀ

በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው ላፍቶ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ላይ ከሃያ ቀናት በፊት ጀምሮ እየደረሰ ያለው ግፍና በደል አሁንም እንደቀጠለ ሲሆን እጂግ በርካታ ወገኖች አሁንም በከፍተኛ በደልና እንግልት ላይ መሆናቸውን አዲስ አበባ የሚገኘው ዘጋቢያችን በላከልን ዘገባ ገለጸ፣ ፣ በአረመኔው የወያኔ አገዛዝ ጨካኝ ርምጃ ቤታቸው የፈረሰባቸውን ነዋሪዎች ያነጋገረው ዘጋቢያችን እንደገለጸው፣ በተለይም ለህሊናቸው ያልተገዙና ለጥቂት ፍርፋሪ ያደሩ ፖሊሶች እያደረሱባቸው ያለውን በደል በሚያሳዝን ሁኔታ የገለጹ ሲሆን ፣ እነዚሁ ተበዳዮች የዘረኛውና አረመኔው ወያኔ ሆድ አደር ፖሊሶች የጭካኔ ተግባራቸውን ባስቸኳይ አቁመው ከወገኖቻቸው ጎን ይቆሙ ዘንድ ተማጽነዋል።

ዘጋቢያችን ካናገራቸው በርካታ ግለሰቦች ውስጥ ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የ 45 ዓመት እድሜ ያላቸው የመንግስት ሰራተኛ እንደተናገሩት፣ ፖሊስ በመሰረቱ ሊቆም የሚገባው ለህዝብ ቢሆንም ይህ መርህ ተጥሶ ከወያኔ ጎን መቆማቸው አዲስ እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ ፖሊሶቹ በንሃን ዜጎች ላይ እየወሰዱት ያለውና ህጻናትን ሳይቀር በቆመጥ እስከመግደል መድረሳቸው በፍጹም ይቅር ሊባል የማይችል በደል ነው ብለዋል፣ ፣ ቀጥለውም እነኝህ ህሊናቸውን የሳቱ ፖሊሶች ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ቆም ብለው ማሰብና እያደረጉ ያለውን ጥፋት በመመርመር ከህዝብ ጎን መቆም እንዳለባቸው አስጠንቅቀዋል።

ዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በላፍቶ ክፍለ ከተማ ሃና ማሪያም እየተባለ በሚተራው አካባቢ እጂግ በርካታ የሞእኖሪያ ቤቶችን በማፍረሱ፣ በአስር ሺዎች የሚቆተሩ ዜጎች ያለመኖሪያ ቤት መቅረታቸው፣ በርካታ ወገኖች መታሰራቸውና መገደላቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## የአፋር ክልል የጸጥታ ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ መምጣቱ ተነገረ

በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ በአፋር ክልል የተፈጠረዉ አለመረጋጋት ያሳሰበዉ የወያኔ አገዛዝ በክልሉ የሚገኙትን ከፍተኛ የፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት አዛዦቹን ከያሉበት አስጠርቶ ሎጊያ በምትባል ከተማ ዉስጥ ካለፈው ሳምንት ቅዳሜ ጀምሮ ስብሰባ መቀመጡን በክልሉ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ይህ አባህና በሚባል ሆቴል የተጠራዉ ስብሰባ ለጋዜጠኞችና ለህዝብ ዝግ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ የጦርና የፖሊስ አዛዦቹ ስብሰባው ዉስጥ የተገኙት የሲቪል ልብስ ለብሰው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። የስብሰባዉ ዋና አጀንዳ በአፋር ክልል የተፈጠረዉ አለመረጋጋትና የጸጥታ መደፍረስ ሲሆን አብዛኛዉ የዉይይቱ ክፍል በክልሉ ጸጥታ፤በመረጃ አሰባሰብና ለእነዚህ ሁለት ስራዎች በሚያስፈልገዉ በጀት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

የከፍተኛ መኮንኖቹ ስብሰባ ሲጠቃለል ባሳለፈዉ ዉሳኔ መሠረት ለአፋር ክልል ጸጥታ አግልግሎትና ለመረጃ አሰባሰብ ስራዎች የሚዉል ከፍተኛ በጀት የተመደበ ሲሆን አምስት የወረዳ አስተዳዳሪዎች ሀላፊነታችሁን አልተወጣችሁም በሚል ሰበብ ከሥልጣናቸው ተባርረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በአፋር ክልል የሚገኘዉ ሙስሊም ማህበረሰብ “አህባሽ” የተባለዉን አስተምህሮ አንቀበልም የሚል ተቃዉሞዉን አሁንም እያሰማ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በደል መሸከም አቃተን ያሉ የአባይ ግድብ ሠራተኞች ፕሮጀክቱን በብዛት እየለቀቁ መሆኑ ተነገረ

በአባይ ግድብ ግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ አያሌ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የወያኔ የበላይ ተቆጣጣሪዎቻቸዉና የውጭ አገር አሰሪዎች የሚያደርሱባቸዉ በደልና ግፍ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመምጣቱ ስራቸውን እየለቀቁ ከአካባቢዉ በመዉጣት ላይ መሆናቸዉን ባህርዳር ዉስጥ የሚገኙት የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ዉስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። በተለይ የግድቡ ግንባታ በተጀመረባቸዉ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ዉስጥ “አባይ ተደፈረ” የሚል አገራዊ ስሜት ፈንቅሏቸዉ ወደ አካባቢው በመጉረፍ ከአስራ ስምንት ወራት በላይ በግድቡ ግንባታ ስራዎች ላይ በንቃት ሲሳተፉ የነበሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ከአሰሪዎቻቸዉ በሚደርስባቸዉ በደል የተነሳ ፕሮጀክቱን እየለቀቁ ወደየመጡበት አካባቢ በመመለስ ላይ መሆናቸዉን ዘጋቢያችን አክሎ የላከልን ዜና ያስረዳል።

አብዛኛዉን የአባይ ግድብ ሠራተኛ ያንገሸገሸዉ በፕሮጀክት ማኔጅመንትና በሠራተኛዉ መካከል ያለዉ የተበላሸ ግንኙነት ሲሆን በተለይ ጣሊያኖቹ ሠራተኞች ለኢትዮጵያዉያኑ ሠራተኞች ያላቸዉን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ!

ከሰሞኑ በህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ቁጥጥር ሥር ያለችው ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አባል ሆና ተመርጣለች። በዚህ አህጉራዊ ኮታን አንጂ የአገሮችን ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሪኮርድ እንደ መመዘኛ በማይወስደዉ ምርጫ ከአፍሪካ አህጉር ኢትዮጵያን ጨምሮ ኩትዲቯር፤ጋቦን፤ኬንያና ሴራሊዮን የጉባኤዉ አባል ሆነዉ ተመርጠዋል። በሰብአዊ መብት ረጋጭነቷ የምትታወቀዉ ኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አባል ሆና የመመረጧ ዜና እንደተሰማ በህወሀትና በደጋፊዎቹ መንደር ሠርግና ምላሽ ሆኖ ሰንብቷል።

የህወሀት ባለስልጣኖቸችና በአለም ዙሪያ የሚገኙ ጀሌዎቻቸዉ ከሰሞኑ እስክስታ ቀረሽ ዘፈን መዝፈን የጀመሩት ኢትዮጵያ ለመንግስታቱ ጉባኤ የተመረጠችዉ የአገሪቱ የስብአዊ መብት ጥበቃ በመልካም ደረጃ ላይ ስለሆነ ነዉ ብለዉ ስለምያምኑ ነዉ። ወንጀላቸዉና በህዝብ ላይ የሚፈጽሙት ግፍና በደል የማይታያቸዉን የህወሀት ባለስልጣኖች ከብዙዎቻችን ልዩ የሚያደርጋቸዉ ባህሪይ ቢኖር ዉሸትን እዉነት ነዉ ብለዉ ስለሚያምኑ ነዉ። ይሄ ደግሞ በሽታ እንጂ ጤንነት አይደለም። አንደ ጵላጦስ እጅን በዉሀ ታጥቦ ከደሙ ንጹህ መሆን አይቻልም።

እዚህ ላይ በአንድ በኩል የሚያስገርሙ በሌላ በኩል ደግሞ የሚያሳዝኑ ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛዉ ኢትዮጵያ የተመድ የስብአዊ መብቶች ጉባኤ ኣባል ሆና የተመረጠችዉ የወያኔ ዘረኞች ደራ ወረዳ ዉስጥ አገርን ጉድ ያሰኘና የሰው ልጆችን ክብር ያዋረደ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈጸሙ ማግስት መሆኑ ሲሆን ሁለተኛዉና አሳዛኙ ነገር ደግሞ የተመድ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በሰዉ ልጆች መብት ረገጭነቷ ቤመድረኩ ላይ ስሟ የሚነሳዉን ኢትዮጵያን ለዚህ በየአገሩ የሚታየዉን የሰዉ ልጅ መብት ጥሰት ለሚከታተለዉ ከፍተኛ አካል አባል አድርጎ መምረጡ ነዉ። ከዚህ ቀደም ኢራንንና ኢራቅን የመሳሰሉ መብት ረጋጭ አገሮች አባል አድርጎ የመረጠዉ የተመድ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በረጂም አመት ታሪኩ ይህ ነዉ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ስራ ሊሰራ ያልቻለዉ ኢትዮጵያን፤ ኢራንንና ጋቦንን የመሳሰሉ የለየላቸዉ መብት ረጋጭ አገሮች አባል አድርጎ ሰልሚመርጥ ነዉ።

የህወሀቷ ኢትዮጵያ የምትታወቀው የሰው ልጆችን መብት በመርገጥ እንጂ በማክበር አይደለም። ፖለቲከኞችን፤ ጋዜጠኞችን፤ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን በማሰርና በማንገላታት ከሚታወቁ አገሮች መካከል ግንባር ቀደሟ የወያኔዋኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ዉስጥ የወያኔን አገዛዝ ተቃውመዋል የተባሉ ዜጎች አሸባሪ ተብለው መታሠር ብቻ ሳይሆን ብልቶቻቸውን ተቀጥቅጠው የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል። አጥበተው ያሳደጉ እናቶች ጡቶች በሽቦ እንዲገረፍ ተደርጓል። በሽብርተኝነት ተከስሰዉ የሚታሰሩ ዜጎች ንብረት ተወርሶ ልጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ለእርዛትና ለድንቁርና ተዳርገዋል። እንግዲህ ይህች ኢትዮጵያ ነች በሰብዓዊ መብት ካውንስል ውስጥ አባል ሁና እንድትቀመጥ የተደረገው።

ኢትዮጵያ የመንግስታቱ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አባል ሆና የተመረጠችዉ ማንም አገር እንደሚመረጠዉ አህጉራዊ ኮታ ለሟሟላት መሆኑ በግልጽ እየታወቀ ሕወሃቶች ግን የተመረጥነው ኢኮኖሚያችን አድጎ ዜጎች በቀን ሦስት ግዜ በልተው ማደር በመቻላቸው፤ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት በመቻሉና ፍትሃዊ ምርጫ ተደርጎ ህዝቡ የመረጠው 99.6% አካል ስልጣኑን መያዝ በመቻሉ፤ዜጎች የልባቸውን ለመናገር ከፍርሃት መውጣት በመቻላቸው ነው እያሉ የገዛ ውሸታቸውን አምነዋል።ዜጎችም የወሮበላዎችን ውሸት እውነት ነው ብለው እንዲያምኑላቸው ደፋ ቀና እያሉ ነው።የገዛ ውሸትን እውነት ብሎ ማመን በሽታ ነው።ህወሃት ደግሞ በዚህ በሽታ የሚሰቃይ ድርጅት ነው።

በአንድ ወቅት በአሜሪካን መንግስት ሰነድ ውስጥ አሸባሪ ተብሎ የተመዘገበው ሕወሃት ከኖረበት ፅልመት ወጥቶ የሰው ልጆችን መብት የሚያከብር ቡድን ይሆናል ብሎ ማመን ለሌሎች ይቅርና ለራሱ ለሕወሃት የሚቻል አይደለም። ህወሃት በተፈጥሮው አሸባሪ ነው።ይህን ተፈጥሮውን መቀየር የሚችል ቡድንም አይደለም። ሕወሃት ከኖረበት ፅልመት ውስጥ ወጥቶ ብርሃን ወዳለበት እንዲመጣ የቆመበትን መሠረት ዞር ብሎ ማየት መቻል ይኖርበታል።ይህ ደግሞ ለግትሮቹ ህወሃቶች የሚቻል አይደለም።የእነርሱ አንገት የተሠራው አዙሮ ለማየት ሳይሆን ያን በብቀላና በጭካኔ የተሞላውን ጭንቅላት ለመሸከም ብቻ ነው።

የተከበራችሁ የአገራችን ዜጎች የሚረዳን ማንም የለም። ክብራችንና ነፃነታችንን የምናስመልሰው እኛው ብቻ ቆርጠን በመታገል ነው።ነፃነታችንን ከዚህ ወይም ከወዲያ ማዶ መጥቶ የሚሰጠን ማንም የለም። ነፃነታችን በእጃችን ነች።ሞት ወይም ነፃነት ማለት ካልቻልን ነፃነት እንዲሁ በደጅ ጥናት የምትገኝ አይደለችም።

በመጨረሻም ይህን ፅልመት የወረረውን የወሮበላ ቡድን ከአገራችን ጫንቃ ላይ አውርደን ወዲያ በመጣል የአገራችንን መልካም ዝና መትከል የኢትዮጵያዊያን ድርሻ ነው።ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ከኢትዮጵያዊያን ውጪ ሌላ ኃይል ከየትም አይመጣምና በየአቅጣጫው የጀመርነውን ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የሰማዕቱ አቡነ ጵጥሮስ ሀዉልት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ፕሮጀክት ሲሰራ እንደዚህ አይነት የታሪክ ቅርሶችን አገናዝቦ ነዉ አንጂ ታሪክ እየተናደ መንገድ አይሰራም ብላዋል፤ በተለይ እንደ አቡነ ጴጥሮስ አይነቱ የአገርና የህዝብ ጀግንነትና መስዋዕትነት ምልክት የሆነ ሰዉ ሀዉልት እንኳን ሊፈርስ በአጠገቡ የዚህን ሀዉልት ታሪክ የሚያሳንስ ምንም ነገር መሰራት የለበትም ብለዋል።

ታላቁ የእምነት ሰዉና አርበኛ አቡነ ጳጥሮስ ፋሺስቶች አርበኞችን አዉግዙና ይፈታሉ ሲሏቸዉ "የአገሬ ሰዎች እነዚህ ፋሺስቶች አርበኞችን ሽፍቶች ናቸዉ ሲሏችሁ አትመኗቸዉ፤አርበኞች ከፋሺስቶች ሽብር ነፃ እንድትወጡ የሚሞቱላችሁ ወንድሞቻችሁ ናቸዉ። ይልቁንም ትክክለኛ ሽፍታ ማለት እነዚህ ከሩቅ አገር መጥተዉ እኔና እናንተ ፊት የቆሙትና አገራችንን ለመግዛትና ነፃነታችንን ለመቀማት የሚታገሉ ፋሺስቶች ናቸዉ። የአገሬ የኢትዮጵያ መሬት የዚህን ወራሪ ጦር አገዛዝ በፍጹም አይቀበልም ያሉ ቆራጥ የሐይማኖት አባት ነበሩ። አቡነ ጴጥሮስ ዛሬ የሐይማኖት አባቶች የፖለቲካ ካድሬ ሆነዉ ህዝብን በሚያስገድሉባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝቤንና አገሬን ከምክድ ሞቴን እመርጣለሁ ብለዉ በሚወዱት ህዝብ ፊት በጥይት ተደብድበዉ የሞቱ የአገራችን የኢትዮጵያ የትግልና የመስዋዕትተነት ምሳሌ ናቸዉ። ዛሬ የወያኔ ዘረኞች እናፈርስለን የሚሉት ይህንን የመሰለ ግዙፍ የታሪካችን አካል የሆነዉን ሀዉልት ነዉ። እዚህ ላይ እጅግ በጣም የሚያሳዝነዉና የወያኔን ዘረኝነት አጉልቶ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ከፍተኛ ተቃውሞ የቀረበበትና በሲኖዶስ እንዲፈርስ የተወሰነው የአቡነ ጳውሎስ ሀውልት ቆሞ የታላቁ አርበኛና መስዋእት የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልት ይፍረስ ነው መባሉ ነዉ።

## ኢሳትን አያችሁ የተባሉ ወታደሮች ታሰሩ፤ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተጨማሪ በሠራዊቱ ዉስጥ ይህ ነዉ የማይባል የኤኮኖሚ ችግር፤ ሰር የሰደደ የዘር ልዩነትና ከፍተኛ የአስተዳደር በደል በየቦታዉ ተንሰራፍቶ ይታያል ብለዋል። መኮንኑ ንግግራቸዉን በመቀጠል አብዛኛው የኢትዮጵያ ወታደር የመከላከያ ሠራዊቱን የሚቀላቀለዉ በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ቢሆንም የሰራዊቱ አባላት በአገሪቱ ከሚታየዉ የኤኮኖሚ ችግር ማምለጥ አልቻሉም ብለዋል። እንደ መኮንኑ አበባል ከኮሎኔልነት በታች ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች ገቢያቸዉ ከተራው ወታደር ብዙም እንደማይለይና ተደማጭነትም እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል።

በወያኔ ሠራዊት ዉስጥ ኮሎኔልና ከኮሎኔል በላይ ሹመት ካላቸዉ መኮንኖች ዉስጥ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑት የህወሀት አባል የሆኑ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ የእነዚህ መኮንኖች ኑሮ ከበታቾቻቸው ጋር ሲነጻጻር ሰማይና ምድር መሆኑን ተራው ወታደር ጭምር የሚያዉቀዉ ጉዳይ ነዉ።በኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ዉስጥ ህንፃና ዘመናዊ ቤቶችን ሰርተው የሚያከራዩት አነዚሁ የህወሀት መኮንኖች ናቸዉ።ለምሳሌ አዲስ አበባ ዉስጥ በወረዳ 17፣ በቦሌ መድህኒአለም አካባቢ ጄኔራል ወዲ አሸብር የ55 ሚሊዮን ብር ህንፃ ያሰራ ሲሆን ኮሎኔል ታደሰና ጄነራል ዮሀንስ የሚባሉ የህወሀት መኮንኖቸች ደግሞ የ12 ሚሊዮንና የ45 ሚሊዮን ብር ህንፃ አሰርተዉ በማከራየት ላይ ናቸዉ።

## የአፋር ክልል የጸጥታ ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የአገዛዙ የጸጥታ ኃይሎች ተቃዉሞዉን አስተባብራችኋል የሏቸዉን ሰዎች ከየቦታዉ እያደኑ በማሰር ላይ ናቸዉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ የጸጥታ ኃይሎች በአፋር ክልል ደጋን በተባለ ቦታ የታሰሩ መሪዎቻችን ይፈቱ ብለዉ የጠየቁትን ሰባት ሰዎች ገድለዉ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሰዎችን ማቁሰላቸዉን ለማወቅ ተችሏል።
በአሁኑ ወቅት በአፋር ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የየከተማዉ መግቢያና መውጪ ኬላዎች በጸጥታ ኃይሎች እየተፈተሹ ሲሆን በክልሉ ከፍተኛ ዉጥረትና አለመረጋጋት ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ ለየት ባለ ዜና እራሳቸውን የሚያቆስሉ የወያኔ ወታደሮች ቁጥር እየጨመረ መሄዱ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል። በተለይ በጄኔራል ሰዓረ መኮንን የሚመራው የሰሜን ዕዝ መከላከያ ሠራዊት አባላት ከፍተኛ ብሶትና ምሬት የሚታይባቸዉ ሲሆን በብዛት እራሳቸዉን የሚገድሉትና የሚያቆስሉትም የዚሁ በጄኔራል ሰዓረ መኮንን የሚመራው የሰሜን ዕዝ መከላከያ ሠራዊት አባላት መሆናቸዉን ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ወታደራዊ ምንጮቻችን የላኩልን ዜና ያስረዳል።

# ላፍቶን አደራ

ለወትሮዉ እንኳን ልቅሶና ኡኡታ ሹክ የሚል ድምጽም ደጋጋግሞ የማይሰማባት ላፍቶ በህፃናት፤በሴቶችና በአረጋዉያን የሰቆቃ ጩኸት እየተተራመሰች ነዉ። እናት የመንፈቅ ልጇን ታቅፋ እንዳታጠባዉ እሷ እራሷ ምግብ ከቀመሰች ሁለት ቀኗ ነዉና ጡቷ ደርቋል፤ እንዳታስተኛዉ ቤቷን የወያኔ ቡልዶዘሮች እንዳልነበረ አድርገዉታል። አባት ሁለት ልጆቹን ታቅፎ አዉላላ ሜዳ ላይ ተኝቷል፤ ልጆቹ ቢነቁ የሚጠይቁትን የዉቃልና ቀኑን ሙሉ ቢተኙ ደስ ይለዋል። እሱም ቢሆን አንኳን የሚበላ “የሚላስ የሚቀመስ” የለዉምና ያለዉ አማራጭ መተኛት ብቻ ነዉ። ምግብ ወይም ስራ ፍለጋ እንዳይሄድ የእሱም መኖሪያ ቤት በወያኔ ቡልዶዘሮች ስለተናደ ሁለት ልጆቹን ጥሎ ዬትም መሄድ አይችልም። የአዲስ አበባ ዉርጭ ሲነጋጋ ያንገበግባል፤ ቀን የፀሐዩ ሙቀት አታምጣ ነዉ፤ ሲመሽ ደግሞ ብርዱ ዛር እንደያዘዉ ሰዉ ያንቀጠቅጣል። ላፍቶ ዉስጥ ልብስ የለም፤ምግብ የለም መጠለያም የለም። እመጫት የመንፈቅ ልጇንና ባዶ ሆዷን ታቅፋ አባት ደግሞ ሁለት ልጆቹን ግራና ቀኝ አስተኝቶ ሁሉም ጧት በዉርጭ፤ ቀን በሀሩር ማታ ደግሞ በብርድ ይጠበሳሉ። ይሄ ሁሉ የፍጥረት ሰቆቃ የሚታየዉ አዲስ አበባ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ነዉ። ላፍቶን የመንግስት ጭካኔ፤ የከንቲባዋ ዝምታና የኗሪዎቿ ጩኸት እረፍት ነስቷታል። አዎ! ላፍቶ በአንድ በኩል በቡልዶዘር ጩኸት፤በሚፈርስ ቤት ጩኸትና ህዝቡን በሚያሸብሩ የፌዴራል ፖሊሶች ጩኸት በሌላ በኩል ደግሞ በህፃናት ልቅሶ፤ በአባቶች ኡኡታና በሴቶችና በአረጋዉያን ጩኸት ተወጥራለች። በንጉስ ሄሮድስ ዘመን “ጩኸት በራማ ተሰማ” ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ ዉስጥ እንደተጻፈ ዛሬም በወያኔ ዘመን ጩኸት በላፍቶ ተሰማ።

ብዙ ህዝብ የሚኖርባት ላፍቶ በወያኔ ዘመን ከተስፋፉት የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎች አንዷ ናት። እንደማንኛዉም የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ላፍቶም ደሀዉ ጎጆዉ ቀልሶ ሀብታም ቪላ ገንብቶ ጎን ለጎን እየተያዩ የሚኖርባት ቦታ ናት። አቅም ካለዉ ላይና ታች አለዚያም እንደአቅምቲ ዛኒጋባዉን ተክሎ የሚኖረዉ የላፍቶ ነዋሪና በፌዴራል ፖሊስ ቪላዉ የሚጠበቅለት የቦሌ ነዋሪ ሁለቱም እኩል ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ። ፌዴራል ፖሊስ ዘራፊዎቹን የወያኔ ሹማምንት እቤታቸዉ ድረስ አጅቦ እያስገባ የላፍቶዉን ደሃ ደግሞ ቤቱን የሚያፈርስበት ምንም ምክንያት የለም። የከተማ ፕላን ወጥቶ ከተማ የሚገነባዉ ለህዝብ ህንጻዎች የሚሰሩትም ሆነ የሚፈርሱት ለህትዝብ ትቅም ሲባል ብቻ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ ሳይሆን ዬትም አገር ዉስጥ የህዝብን ጥቅምና ፍላጎት የሚጻረር ምንም ነገር አይሰራም ወይም አይፈርስም። ይህ በብዙ አገሮች ዉስጥ የሚሰራ ህግ ወያኔ በሚመራት ኢትዮጵያ ወስጥ አይሰራም። ኢትዮጵያ ዉስጥ የህዝብ ጥቅም ቢነካ ባይነካ የወያኔ ባልስልጣኖችና ጓደኞቻቸዉ አይን ያረፈበት ቤት ወይም ህንፃ ሰበብ ተፈልጎለት ይፈርሳል።የወያኔ ካድሬና ሹም ካልፈለገዉ በከፍተኛ ወጪ የተሰራ መንገድ ይፈርሳል ወይም መሰራት የሌለበት መንገድ ይሰራል።

በቅርቡ የወያኔ ግፈኞች አላግባብ ቤት ሰርታችኋል ብለዉ ቤታቸዉን የፈረሱባቸዉ አባ ወራዎች ብዛት ለ17 ሺ ባላይ ነዉ፤ ይህ ቁጥር ደግሞ አባ ወራዎቹን ብቻ አንጂ እናቶችን፤ህጻናትንና የቅርብ ቤተሰብ አባላትን አያጠቃልልም። በፊዉዳሉ ስርአት ዉስጥ የመሬት ከበርቴዉ የጭሰኛዉን ጎጆ አፍርሶ የራሱን ይዞታ እንደሚያስፋፋ ሁሉ ዛሬም ወያኔ የከተሜዉን ቤት እያፈረሰ ቦታዉን የኔ ለሚላቸዉ ስግብግቦችና ለሆዳችዩ ላደሩ ምስለኔዎች እየሰጠ ነዉ። ወያኔ እንደለመደዉ ቤቱ የተሰራዉ ከህግ ዉጭ ነዉ እያለ ቢዋሽም በታቸዉ የፈረሰባቸዉ ሰዎች አንደተናገሩት ቤታቸዉን የሰሩት መንግስት ፈቅዶ ነዉ ወይም ቤቶቹ ሲሰሩና ተሰርተዉ አልቀዉ ቅዶ ነዉ ወይም ቤቶቹ ሲሰሩና ተሰርተዉ አልቀዉ ነዋሪዎቹ ሲገቡ ነዋሪዎቹ ሲገቡ ወያኔ ያዉቅ ነበር። ባያዉቅስ? መንግስት ደፈርከኝ ብሎ ህዝብን የሚበቀል አካል አይደለም። የ60 ሺ ዜጎችን መኖሪያ ቤት አፍርሶ ነዋሪዎቹን ሜዳ ላይ የሚበትን መንግስት እንኳን ኢትዮጵያ ዉስጥ በአለማችንም የታየዉ በአፓርታይድ ደቡብ አፍሪካና በቀድሞዋ ሮዴሺያ ዉስጥ ብቻ ነዉ። እነዚህ ሁለት አገሮች ደግሞ ዘረኝነት የነገሰባቸዉ አገሮች ነበሩ። ይህንን ያክል ህዝብ ለአገር ጥቅም ሲባል መፍረስ ካለበት በመጀመሪያ ዜጎቹ የሚኖሩበት ቦታ ተፈልጎ መገኘት አለበት እንጂ የሰዉ ልጅ እንደለማዳ እንስሳ ከመኖሪያ ቤቱ ተገፍቶ ወጥቶ አይኑ እያየ መኖሪያ ቤቱ በቡሉዶዘር አይናድም። ለማዳ እንስሳ እንኳን ሌላ ቤት ይሰራለታል እንጂ ባዶ ሜዳ ላይ አይጣልም። ወያኔ ዘረኛ ነዉ የሚባለዉ ለካስ እንደዚህ የኔ አይደሉም የሚላቸዉን ዜጎች ከእንስሳ አሳንሶ ስለሚያይ ነዉ።

ወያኔ ስሙ በተነሳ ቁጥር የሚዘገንነን ጭካኔዉ ብቻ አይደለም። ምንም አይነት የህዝብ ስሜት የማይገባዉና ለህዝብ የሚያዝን ልብ የሌለዉ የደነዞች ስብስብ መሆኑ ነዉ። በቅርቡ ላፍቶ ዉስጥ ፖሊስ ወላጆቻቸዉ ፊት በዱላ ቀጥቅጦ የገደላቸዉ የሁለት ህጻናት አሳዛኝ ሞት የሚያሳየን ይህንኑ የወያኔ ጭካኔና ለአገርና ለህዝብ የሚያሳየዉን ግድየለሽነት ነዉ። ለወትሮዉ “በአቡዬ” ና “በማሪያም” ስም የሚማጸነዉ የላፍቶ ህዝብ እነዚህ ደነዞች ቢገባቸዉ ብሎ የዚያን የደሃ አባት ተብሎ የተነገረለትን መሪ ፎቶ በደረቱ ታቅፎ ነበር የለመናቸዉ፤ ችግሩ የቤታቸዉ መፍረስና የእነሱና የልጆቻቸዉ መንገላታት የዚሁ ፎቶዉን የተሸከሙት ሰዉ ራዕይ ስለሆነ የሚሰማቸዉ ጠፋ።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝም ቢሆን ለመለስ ዜናዊ ራዕይ ግብ መምታት ቆርጦ የተነሳ ሰዉ ስለሆነ እንኳን የህዝብን ጩኸት ሰሞኑን በተደጋጋሚ ስሙን ያነሳዉን ፈጣሪ ድምፅም የሚሰማ አይመስልም። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳም ቢሆን ስማ ተብሎ የተነገረዉን ብቻ እንጂ ከትዕዛዝ ዉጭ ምንም ነገር የሚሰማ ጆሮ የለዉም። ፈጣሪም ቢሆን ከላይ ሆኖ ይመለከታል እንጂ በታላቅ ስሙ ስላልተለመነ አይሰማቸዉም። ታዲያ የላፍቶን ህዝብ ጩኸትና ልቅሶ ማን ይስማ?

ላፍቶ ዉስጥ ቤታቸዉ የፈረሰባቸዉ ከ30 ሺ በላይ አባወራዎች ባለፈዉ ሳምንት ከንቲባዉ ቢሮ በዚህ ሳምንት ደግሞ ጠ/ሚኒስትሩ ቢሮ ቀርበዉ አቤቱታቸዉን ማሰማት ቢሞክሩም ከጠ/ሚኒስትሩም ሆነ ከከንቲባዉ የተሰጣቸዉ ምላሽ በፓሊስ መደብደብና መታሰር ብቻ ነበር። ዛሬ በየመንገዱና በየአደባባዩ ተበታትነዉ የሚኖሩት የላፍቶ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ሁሉም ተማሪዎች ናቸዉ፤ ሆኖም እነዚህ ተማሪዎች ዛሬ እንኳን ት/ቤት ሊሄዱ ገላቸዉን ታጥበዉ ልብስ የሚቀይሩበት ቦታ የላቸዉም። የሚገርመዉ እነዚህ ወጣቶች ተወልደዉ ያደጉት ዛሬ ወያኔ ህገወጥ ናቸዉ ብሎ ባፈረሳቸዉ ቤቶች ዉስጥ ነዉ። እነዚህ ቤቶች ከአስር አመት በላይ የቤት ግብርና የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ የተከፈለባቸዉ ቤቶች ናቸዉ። ዘረኞቹ የወያኔ ገዢዎች ሊነግሩን እንደሚሞክሩት የፈረሱት ቤቶች ህገወጦች ከሆኑ እንዴት መብራት ገባላቸዉ? እንዴትስ የመንግስት ግብር ሰብሳቢዎች አወቋቸዉ? ቤቶቹ ህግወጦች ናቸዉ ብለን ብናምን እንኳን ምን አይነት መንግስት ነዉ ከ30 ሺ በላይ አባወራዎችንና ቤተሰቦቻቸዉን ሜዳ ላይ በትኖ ቤታቸዉን የሚያፈርሰዉ? ለዚያዉም ወያኔን የመሰለ 99.6% የህዝብ ድምጽ አገኘሁ ብሎ የሚፏልል መንግስት!

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ በወያኔ ዘረኞች ሰብዓዊ መብቱ ያልተረገጠ ዜጋ ወይም ወያኔ ያላዋረደዉ የህብረተሰብ ክፍል የለም። ወላጆች ልጆቻቸዉ ፊት ተገድለዋል፤ ህፃናት ከእናቶቻቸዉ እቅፍ ተነጥቀዉ በዱላ ተቀጥቅጠዋል። ወጣት ተማሪዎች ለምን ሠላማዊ ሠልፍ አደረጋችሁ ተብለዉ በአደባባይ ተረሸነዋል። ጋዜጠኞች ለምን ጻፋችሁ ተብለዉ ታስረዋል፤ ተደብድበዋል ከአገር ተሰድደዋል። ከወያኔ ጋር ንኪኪ የሌለዉ ነጋዴ የንገድ ፈቃዱ ስለማይታደስ ከስሮ ንግዱን ዘግቷል። ከወያኔ ካድሬዎች ጋር የማይተባበር ገበሬ የማዳበሪያ፤የምርጥ ዘርና የፋይናንስ አገልግሎት ስለሚከለከል በገዛ አገሩ ባይተዋር መሆኑን ጠልቶ ወደ ጎረቤት አገሮች እየተሰደደ ነዉ። የአህአዴግን የአባልነት ፎርም አንሞላም ያሉ ሰራተኞች ከስራቸዉ ተባርረዋል። በዘረኛ የህወሀት መኮንኖች የሚታዘዘዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ምድር ሲኦል ሆኖበታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ጥቂት ዘረኞች እየረገጡ ሊገዙን 17 አመት መስዋዕትነት የከፈሉ ከሆነ የእኛ 21 አመት ሙሉ አንገት ደፍቶ መገዛት ከዉርድም ዉርደት ነዉ። እነሱ በዘር ከፋፍለዉ ሊገዙንና አገራችንን ሊበታትኑ የከፈሉትን መስዋዕትነት እኛ የአገራችንን አንድነት ለመጠበቅና ነፃነታችንን ለማስከበር የማንከፍልበት ምንም ምክንያት የለም። የዛሬዉ የወያኔ ግፍ ሰለባ ላፍቶ ስለሆነች እንደምሳሌ አቀረብናት እንጂ የእነዚህ ዘረኞች ግፍና በደል የጀመረዉ እግራቸዉ አዲስ አበባን የረገጠ ቀን ነዉ። አርሲና ሐረር ዉስጥ ሲጨፈጭፉን ዝም አልናቸዉ . . . አኝዋክ ላይ ደገሙን። አኝዋክ ላይ በአንድ ጀምበር ከ400 ሰዉ በላይ ሰጨፈጭፉ ዝም አልናቸዉ አምቦና አዋሳ ላይ መጡብን። ሐረር፤ አርሲ፤ ጋምቤላ፤ አምቦና አዋሳ ላይ ህዝብ እንደ እንስሳ ሲታረድ እኛም ሆነን አለም አቀፉ ህብረተሰብ ያሳየዉ ዝምታ የልብ ልብ ሰጥቷቸዉ የአዲስ አበባን መንገዶች የዉግያ ወረዳ አስመስሏቸዉ። ይህንን ሁሉ ግፍና በደል ያደረሰብን ግለሰብ ዛሬ በህይወት ባይኖርም እሱን የተካዉ ሰዉ የእሱን ራዕይ ለማስፈጸም የቆረጠ ሰዉ ነዉና ይህ ዘረኛ ሰዉ የጀመረዉ ግፋና ጥፋት ዛሬም እንደቀጠለ ነዉ።

ቱኒዝያ፤ ግብፅ፤ ሊቢያና የመን ዉስጥ አምባገነን መሪዎችን ጠራርጎ ያጠፋዉ የአረቡ አብዮት ቱኒዝያ ዉስጥ ሲፈነዳ የቱኒዚያን ህዝብ በቃ ብሎ ያነሳሳዉ የመሐመድ ቦአዚዝ መስዋዕትነት ነዉ። እኛ አንድ መሐመድ ሳይሆን በሺዎች የሚቆጠሩ መሐመዶችን ሰዉተናል። የኔሰዉ ገብሬና ጓደኛዉ ግርማ ወ/ማሪያም እንደ መሐመድ ቦአዚዝ እራሳቸዉን ሰዉተዋል። መሀል አዲስ አበባ ዉስጥ 200 ሰዎች ዉድ ህይወታቸዉን ሰጥተዉናል; አሁን በቅርቡ ደግሞ ወሎ ዉስጥ የእስልምና እምነት ተከታይ ወንድሞቻችን መሲጊድ ዉስጥ ተገድለዋል። ወያኔዎች ይህ ሁሉ አልበቃ ብሏቸዉ ከሰሞኑ የላፍቶን ነዋሪ ቤቱን እላዩ ላይ አፍርሰዉ ሁለት ገና በእግራቸዉ ቆመዉ መሄድ ያልጀመሩ ህፃናትን ከወላጅ እናታቸዉ እቅፍ ነጥቀዉ በዱላ ደብድበዉ ገድለዋል። ታድያ ከዚህ በላይ ምን እስኪያደርጉን ድረስ ነዉ የምንጠብቀዉ? ይህ ዝምታ የጤና አይመስልም . . . . እንኳን ሰዉ ወተተም ሲበደል ይሸፍታል።

ከሁለት አማራጮች አንዱን መምረጥ የግድ ነዉ። ታግሎ ነፃ መዉጣት ወይም እየተገዙ መኖር። ለነጻነት የሚከፈለዉ ዋጋ ምን ግዜም ቢሆን ትልቅ ነዉ ሆኖም የየዘመኑ ኢትዮጵያዉያን ይህንን ትልቅ ዋጋ እየከፈሉ አልፈዋል። ዛሬ የኛ ተራዉ የኛ ነዉ። እኛ ኢትዮጵያዉያን የማንመርጠዉ አማራጭ ቢኖር በቃኝ ብሎ እጅ መስጠትን ወይም ተሸንፎ መኖርን ነዉ። እነሱ ጥቂቶች እኛ ብዙኋን ነን። እነዚህን ዘረኞችና የገነቡትን ስርአት ለመደምሰስ የብዛታችንን ያክል መሰለፍ የለብንም። የሚያስፈልገን አንድ ነገር ብቻ ነዉ እሱም በገጠርም በከተማም ለወያኔ አልገዛም ማለት ብቻ ነዉ፤ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከአሁን የተሻለ ግዜ የለምና በአንድ ላይ እንነሳ!

## ሲጀመር በህዝብ ያልታወቀው የህውሃት ማዕከላዊ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የህወሀት መሪዎች፤ ነባር አባላትና ደጋፊዎች የጠ/ሚኒስትርነቱንና የምክትል ጠ/ሚኒስትርነቱን ቦታ ባለማግኘታቸዉ ክፉኛ በመደናገጣቸዉ አዲሱን ሹመት አንቀበልም እስከማለት ድረስ መድረሳቸዉ ይታዋሳል።

ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ ሰሞኑን መቀሌ ዉስጥ ባካሄደው ስብሰባ አብዛኛዎቹ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የተገኙ ሲሆን ከነባር አባላቱ ዉስጥ አሜሪካ ዉስጥ በሕክምና ላይ የሚገኘዉ ስዩም መስፉን አንዳልተገኘ ታዉቋል። ከመለስ ዜናዊ ሕልፈት በኋለ እንኳን አገር መምራት እንደ ፓርቲና እንደ ግንባር አንድ ቋንቋ መናገር ያልቻለዉ ህወሃት ሦስት ቦታ መከፋፈሉንና አንዱ ቡድን የሌላዉን ቡድን ዉሳኔ እንደማይቀበል ከውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ በቅርቡ የአየር ሃይሉ አዛዥ ጀነራል ሞላ ኃ/ማሪያም ተነስቶ በምትኩ የህወሃቱ ጀነራል መሃሪ ዘውዴ መሾሙን የሚቃወም የህወሃት ቡድን በመነሳቱ ሹመቱ ሳይጸና ቀርቷል። በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ አንድ የህወሃት ማእከላዊ ኮሚቴ አባል በገዛ ፈቃዱ ከፓርቲው  የኋላፊነት ቦታ እራሱን ያገለለ ሲሆን አንድ ሌላ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ደግሞ ፓርቲዉን ለቅቆ ወደ ምድረ አሜሪካ ተጉዟል።

## በደል መሸከም አቃተን ያሉ የአባይ ግድብ ሠራተኞች

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ንቀት በግልጽ ማሳየታቸዉ ብዙዎቹን ወጣቶች እንዳስቆጣ ለማወቅ ተችላል። ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢዉ ሙቀት፤ በሽታና የምግብ አለመስተካከል ሠራተኛዉ የስራ ማቆም አድማ እንዲያደርግ እንዳስገደደዉ ከፕሮጀክቶ አካባቢ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። አንድ ስራዉን ለቅቆ የወጣ ወጣት ለዝግጅት ክፍላችን በሰጠዉ ቃለምልልስ በእነዚህና በሌሎችም የተለያዩ ችግሮች የተነሳ በየቀኑ ከ40 እስከ 50 የሚደርሱ ሠራተኞች ስራቸዉን እየለቀቁ ወደየመጡበት አካባቢ እንደሚመለሱ ተናግሯል። የወያኔ አገዛዝ ግድቡ በእቅድ በተያዘለት የግዜ ገድብ ዉስጥ ይጠናቀቃል እያለ ቢናገርም በሠተኞች ስራቸዉን እየለቀቁ መሄድ፤ በማኔጅመንት ችግርና በገንዘብ እጥረት የተነሳ የአባይ ግድብ በአስር አመት ዉስጥም እንደማይጠናቀቅ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ኤክስፐርቶች በመናገር ላይ ናቸዉ። በቅርቡ አለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም የአባይ ግድብ ፕሮጀክት በአገሪቱ ኤኮኖሚ ላይ የፈጠረዉን አሉታዊ ተፅዕኖ በመጥቀስ የኢትዮጵያ መንግስት የህዳሴዉን ግድብ ፕሮጀክት እንዲከልስ ማስጠንቀቁ አይዘናጋም።

## ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ኢትዮጵያ ኑክሌር ኤነርጂን ለመጠቀም ቁርጠኛ ናት ማለቱ ተሰማ

ኢትዮጵያ ኑክሌር ቴክኖሎጂን ሰላማዊ  ለሆኑ የልማት ስራዎች ለመጠቀም ቁርጠኛ ናት ሲል  ሀይለማርያም ደሳለኝ መናገሩን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ገለጸ። ሃለማሪያም ይህን አስገራሚና ግራ የሚያጋባ ንግግር የተናገረዉ የአለም አቀፉ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ጃፓናዊዉ ዩኪያ አማኖን ሰሞኑን ቤተመንግሰት ዉስጥ ተቀብሎ ባነጋገረበት ወቅት ነው። እንደማንም አገር ኑክሌር ኤኔርጂን የመጠቀም መብት አለን ያለዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ኑክሌርን ለሰላማዊ አገልግሎት ብቻ በመጠቀም ረገድ ኢትዮጵያ የአለም አቀፉ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ጋር ተባብራ ለመስራት ዝግጁ መሆኗን ለዋና ዳይሬክተሩ ለዩክያ አማኖ አረጋግጧል።

ኢትዮጵያ የኑክሌር ቴክኖሎጂን ለመቀጠም የሚያስችላትን ሥርዓትና መዋቅር ለመዘርጋት በኤጀንሲው በኩል የተዘጋጀውን የስምምነት ፕሮቶኮል ለመፈረም በዝግጅት ላይ ናት ያለዉ ሀይለማርያም ደሳለኝ በማግስቱ የኢራኑን የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አሊ አክባር ሳሊህን በጽ/ቤቱ ተቀብሎ አናግሯል። ኢትዮጵያ ኑክሌር ቴክኖሎጂ ለመገንባት እዉቀቱም ሆነ ገንዘቡ የሌላት ቢሆንም ሀይለማርያም ስለኑክሌር አጣቃቀም ባወራበት ማግስት የኢራንን ከፍተኛ ባለስልጣን ተቀብሎ ማናገሩ ብዙዎችን ግራ አጋብቷል። ኢራን የኑክለር ተቋም ግንባታን አስመልክቶ ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ በተለይ ከአሜሪካና ከእስራኤል ጋር አደገኛ ፍጥጫ ዉስጥ መሆኗ የሚታወቅ ነዉ።

“የምትለብሰዉ የላት የምትደርበዉ አማራት” እንደሚባለዉ በሳይንሳዊ ምርምር ስራዎች እጅግ ወደኋላ የቀረችዉና በረሀብ የሚሰቃየዉን ህዝቧን ካለዉጭ እርዳታ መመገብ የማትችለዉ ኢትዮጵያ ስለኑክሌር ቴክኖሎጂ አጠቃቀም መወራቱ ብዙዎችን ያስገረመ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች የተለያዩ ምንጮችን ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጸዋል። በተለይ አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ የአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ምሁር አንደተናገሩት “ኑክሌር ፊዚክስን” በዲፓርትመንት ደረጃ የሚያስተምር ፋኩልቲም ሆነ አስተማሪዎች የሌላት ኢትዮጵያ ስለኑክሌር ቴክኖሎጂ አጠቃም ማዉራት መጀመሯ የአለም ዋንጫ ማጣሪያን የወደቀ ቡድን ዋንጫዉን አገኛለሁ ብሎ እንደማዉራት ያክል ነዉ ብለዋል። እኚሁ ምሁር ንግግራቸዉን በመቀጠል ኢትዮጵያ ኑክሌር ኤኔርጂን የመጠቀም መብቷ የተጠበቀ ቢሆንም የአሁኑ ቅድሚያዋ ግን የተራቡ ልጆቿን መመገብና ወጣት ልጆቿን ማስተማር ነዉ ብለዋል።

## ዘረኝው የወያኔ አገዛዝ በሰብአዊ መብቶች ላይ እየፈጸመ ያለውን ጥሰት በስፋት ቀጥሏል

ገርጂ አካባቢ እጂግ በርካታ ቤቶች መፍረሳቸውን ተከትሎ መኖሪያ ቤቶቻቸው በፈረሱባቸው ዜጎቻችን ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እየተፈጸመ መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

ዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ ከሳምንት በፊት ላፍቶ እየተባለ በሚጠራው ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦችን ሜዳ ላይ በጭካኔ ከበተነ ወዲህ፣ የጥፋት አድማሱን አስፋፍቶ ካለፈው አርብ ጀምሮ ደግሞ በገርጂ አካባቢ የሚገኙ ከ2 ሺህ በላይ ቤቶችን በማፍረስ ነዋሪዎች እጂግ አሳዛኝ በሆነ ችግር ላይ እንዲወድቁ ማድረጉን ዘጋቢያችን አያይዞ ገልጿል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዘገባ ቤቶች በሚፈርሱበት ጊዜ ፖሊሶች በአካባቢው ሰዎች ላይ ከፈጸሙት ድብደባ በተጨማሪ የአገዛዙን ድርጊት የተቃወሙ 20 ወጣቶችን ይዘው ማሰራቸውንና  አንዲት ነፍሰጡር ደግሞ ቤቷ በላዩዋላይ ሲፈርስባት በመመልከቷ ራሱን ስታ መሞቷን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሊቪዥን ኢሳት ዘግቧል።

እንደ ኢሳት ዘገባ በርካታ የሆኑ ነዋሪዎች ልጆቻችንን ከጅብ  ለመታደግ ቀይ መስቀልና የኢትዮጵያ ህዝብ ይድረሱልን በማለት ጥሪ ማድረጋቸውን ያደረገውን ቃለምልልስ ዋቢ በማድረግ አቅርቧል፡፡

ቀደም ብሎ ከሳምንት በፊት በላፍቶ ክፍለ ከተማ በተመሳሳይ ሁኔታ ቤቶች እንዲፈርሱ በመደረጋቸው በርካታ ሰዎች መሞታቸው መታሰራቸውና እጂግ በርካቶች ደግሞ በወያኔው አገዛዝ ወታደሮች ቁም ስቅላቸውን ማየታቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## ብርሃነ ገ/ክርስቶስና የስራ ባልደረቦቹ በድፕሎማቶች ሹመት ላይ ሲፋጩ ዋል

የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠባባቂ ሚኒስትር ብረሃነ ገ/ክርስቶስ የወያኔ/ኢሕአዲግ አባላት ከሆኑት ዲፕሎማቶች ጋር ስድብ ቀረሽ ዉዝግብ ዉስጥ ገብቶ መሰንበቱን ለዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቅርበት ያላቸዉ ምንጫቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። የወያኔዉን ቱባ ሹም ብረሃነ ገ/ክርስቶስና ዲፕሎማቶቹን ጭቅጭቅ ዉስጥ የከተቷቸዉ የተለያዩ ምክንያቶች ቢሆኑም ዋነኛዉና ሳምንት ሙሉ ሲያጨቃጭቃቸዉ የከረመዉ የወያኔ/የኢሕአዲግ አባላት ያልሆኑ ዲፕሎማቶች ለስራ በመታጨታቸው ነው። በተለይ ባለፈዉ ሳምንት ብረሃነ ገ/ክርስቶስና የበታቹ ነጋ ፀጋዬ በተገኙበት ስብሰባ ላይ የተገኙት ድፕሎማቶች ሁሉም የወያኔ/ኢህአዴግ አባላት ሲሆኑ ከፍተኛ አለመግባባት የተፈጠረዉም በዚሁ ስብሰባ ላይ እንደነበር ዘጋቢዎቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል።

በዚህ ብረሃነ ገ/ክርስቶስ በመራዉ ስብሰባ ላይ ትልቅ የሀሳብ ልዩነት የተፈጠረዉ ኢትዮጵያ የወቅቱ  የአፍሪካ ሕብረት ተረኛ ለቀመንበር ከመሆኗ ጋር በተያያዘ መንግድ ነዉ።የአፍሪካ ሕብረት የወቅቱ ለቀመንበርነት ቦታ በመጪው ጥር ኢትዮጲያ እንደምትቀበል በመረጋገጡ  አንጋፋዋ ዲፕሎማት ቆንጂት ሥነ ጊዮርጊስ ለቦታዉ ይመጥናሉ ብለዉ ያቀረቧቸዉ ሦስቱ ግለሰቦች የፓርቲ አባላት ባለመሆናቸው በስብሳበዉ ላይ የነበሩትን የወያኔ/የኢሕአዴግ አባላት ክፉኛ አስቆጥቷል።አምባሳደር ብረሃነ ገ/ክርስቶስ የአንዳፋዋን ዲፕሎማት የቆንጂት ስነጊዮርግስን የስራ ልምድና ለአገራቸዉ ያደረጉትን አስተዋፅኦ በመዘርዘር ስለ አስፈላጊነታቸው ሲያነሳ ይበልጥ ተቃውሞ እንደገጠመው ለማወቅ ተችሏል። ባጠቃላይ ብረሃነ ገ/ክርስቶስ ስብሰባውን በፈለገዉ  ሠዓት ለመጨረስ ችግር የገጠመዉ ሲሆን የእንኳን ከተሰብሳቢው እንዳልተፈቀደላቸው የተገኘው ዜና ያብራራል መስሪያ ቤቱን የመምራት ብቃጠመዉ ሲሆን ት የለህም እስከመባል መድረስም ተመልክቷል። ከምርጫ 97 በኋላ ልምድና ዕውቀት ያላቸው ዲፕሎማቶች መስሪያ ቤቱን ጥለው በመሄዳቸው ከ 200 በላይ የኢሃዲግ አባላት ሥልጠና ተሰጥቷቸው ውጭ ጉዳይን መቀላቀላቸውን መረዳት ተችሏል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB  በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz

በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org